# የፎቶ ፖለቲካ

ታሪኩ አባዳማ መጋቢት 2001

በቀዶ ጥገና የጠሉትን አውጥቶ የወደዱትን ተክቶ በፎቶ ፕሮፓጋንዳ መሥራት ቀላል በሆነበት ዘመን ውስጥ እንገኛለን። አብዛኛው ህብረተሰብ ፎቶ አይዋሽም የሚል እምነት አለው። እና ተቀናቃኝን ወይም ጠላትን በፎቶ አስረጅነት ለማጥላላት ወይም ዋጋ ለማሳጣት ሰፊ የፕሮፐጋንዳ ተግባር ሲፈፀም ታዝበናል።

የፅሁፌ መነሻ በቀዶ ጥገና ፎቶን ለመቀየር ስለሚደረገው ሸፍጥ ለመተንተን አይደለም። ይልቁንም እነ እገሌ ከነ እገሌ ጋር የተነሱት ፎቶ በሚል ዜጎችን ለማንኳሰስ (ridicule) እየተካሄደ ያለውን ጥድፊያ አጠር ባለ መልኩ ለመተቸት ነው። በዚህ ጉዳይ ዙርያ ብዙ ምሳሌዎችን ማስታወስ የሚቻል ቢሆንም ትችቴ በቅርቡ በዶር ያዕቆብ ላይ ያነጣጠረ በኢሕአፓ (ደብተራው?) ድረ-ገፅ ላይ የተለጠፈ ፎቶ ላይ ያተኩራል። ቀደም ባሉት አመታት በዶር ብርሀኑ ነጋ ላይ ተመሳሳይ ዘመቻ በዚሁ ድረ-ገፅ ላይ ተካሂዶ እንደነበር አስታውሳለሁ።

ዶር ያዕቆብም ሆነ ዶር ብርሀኑ አሁን በስልጣን ላይ ከሚገኙ ወይንም ቀድሞ በስልጣን ላይ ከነበሩ ወያኔዎች ጋር ፎቶ መነሳታቸውን የሚያመለክት ተጨባጭ ምስል እንድናይ ተደርጓል። የፎቶ ለጣፊዎቹ አላማ እነኝህ ግለሰቦች ከጠላቶቻችን ጋር ወዳጅ እንደነበሩ ወይንም እንደሆኑ ለማሳወቅ የተደረገ ጥረት ነው። ጥረታቸውን ሳላደንቅ ባላልፍም ፣ ፎቶ በመስቀል እነ ዶር ያዕቆብን ለማሳቀል መሞከሩ ግን ደካማ ጎን እንዳለው ለማሳየት እወዳለሁ። በዚህ ረገድ የፖለቲካ ተቀናቃኞች ብቻ ሳይሆኑ በፖለቲካው አለም ለመጠፋፋት የሚያደቡ ጠላቶች ሳይቀሩ ባንድ አጋጣሚ ተገናኝተው የሚነጋገሩበት በዚያውም ፎቶ የሚነሱበት ሁኔታ አዲስ ነገር እንዳልሆነ ብሎም በፎቶው ላይ የሚታዩት ፖለቲከኞች አንዱ ለሌላው መንበርከኩን ወይንም መማረኩን የማያመለክት መሆኑን ከቅርብ ግዜ ማሰረጃ በማጣቀስ ለማሳየት እሞክራለሁ።

በሁለተኛው አለም ጦርነት ዋዜማ የምዕራቡ አለም እጅግ አድርጎ ይሰጋበት የነበረው ውጥረት በስታሊን የሚመራው የሶቭየት ኮምኒስት እንቅስቃሴ ያሳደረው ስጋት እንደሆነ ብዙዎቻችን የምናስታውሰው ነው። ከናዚ ጀርመን ይልቅ እንግሊዞችም ሆኑ አሜሪካኖች የኮምኒዝምን አደጋ ለመቆጣጠር የሚቻልበት ሁኔታ እጅግ ያሳስባቸዋል። ሂትለር እና ስታሊን በ1941 ላይ የደረሱበት ያለመጠቃቃት ስምምነት ደግሞ የወቅቱን የምዕራቡን አለም ስጋት ይበልጥ አባብሶት ነበር። ይሁንና ሂትለር ፖላንድን ወርሮ የሶቭየትን ድንበር ሲያንኳኳ ስምምነቱ ያከትማል ፤ የጨዋታው ሕግ ይለወጥና ወዳጆቹ ለመጠፋፋት ጦር ይሰብቃሉ። ይህን አጋጣሚ ያጤኑት ምዕራባውያን እጅግ አድርገው ከሚጠሉት እና ሊያጠፉት ከሚመኙት ስታሊን ጋር ወዳጅነት ለመፍጠር ግዜ አላባከኑም። በውጤቱ አለም ከናዚ ጥፋት ድናለች ፤ የእንግሊዙ ዊንስተን ቸርችል ፣ የአሜሪካው ሩስቬልት እና የሶቭዬቱ እስታሊን ባንድ ረድፍ ቆመው ፅዋ በመቃመስ ፎቶ ተነስተው ትብብራቸውን አረጋግጠዋል። የስታሊን እና ምዕራባውያን ወዳጅነት በሁለቱም ወገን ስልታዊ ስለነበር ከጦርነቱ ማግስት ብዙ አለመቆየቱ ይታወቃል።



የእንግሊዝ ወይም የአሜሪካ ሕዝብ መሪዎቹ ከስታሊን ጋር መቀራረባቸው ፣ ያውም ፎቶ መነሳታቸው አላስቀየመውም። አጥፊና ጠፊ የሆኑት የፖለቲካ ወገኖች አብረው ፎቶ መነሳታቸው ፣ ግዜያዊ ወዳጅነት መፍጠራቸው አልተኮነነም ፣ ድርጊቱ አልተወገዘም። በተመሳሳይ መልኩ ብዙ ማለት ይቻላል። የፍልስጤም ነፃነት መሪ ያሲር አራፋት ከእስራኤሉ ጠቅላይ ሚንስትር ኢሁድ ባራክ ጋር አንድ ገበታ ቀርበው ተቋድሰዋል ፣ ፎቶ ብቻ አይደለም ዜናው ለአለም ተብራርቶ እንዲቀርብ ፊልም ተቀርፁዋል።



የሁለቱም አገር ሕዝቦች በፎቶው ወይም በፊልሙ የተነሳ መሪዎቻቸውን ለመወንጀል ወይም ለማውገዝ አልተነሱም። ዕለት ተለት በችግር የሚንገላታው ዜጋ ሁነኛ መፍትሔ እንዲበጅለት ይሻል ፤ ዘላቂ ሰላም መፍጠር ምን ያህል አድካሚ እና አርቆ አስተዋይነት ፤ ብሎም ቀናነት እና ትዕግስተ እንደሚጠይቅም ይገነዘባል - መሪዎቹ ከጠላት ጋር ሳይቀር ለሰላም ሲሉ ሸንጎ መቀመጣቸው ተገቢ እንደሆነ ያምናል።

ስለ ሰላም ለማውጋት ወይንም ለመደራደር ለሰላም መታጣት ምክንያት የሆኑ ወይንም የደፈረሰውን ለማጥራት የድርሻችንን እንስራ የሚሉ  ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የማይግባቡ አቋሞች መገናኘት ይኖርባቸዋል። እንኳንስ ያንዲት አገር ልጆች ቀርቶ በባህል እና በቋንቋ የማይተዋወቁ ሁሉ ችግር ሲከሰት ተቀራርበው መላ ማፈላለጋቸው የማይቀር ነው። ቴክኖሎጂ በፈጠረው ከነፋስ የፈጠነ የመገናኛ ጥበብ አለማችን ወደ ትንሽ መንደር እየተለወጠች ባለችበት ዘመን የኩርፊያ እና የቂም ፖለቲካ ብዙ ቦታ ያለው ነገር አይደለም።

እውቁ አርበኛ ራስ አበበ አረጋይ በጠላት ዘመን ከፋሽስት ኢጣልያ ሹማምንት እና ከራሳቸው ጭፍሮች ጋር የተነሱት ፎቶ የአርበኝነት ታሪካቸውን ሲያጎድፈው ሰምቼ አላውቅም። እንደሚባለው ጣልያን ራስ አበበ አረጋይን አባብሎ እጅ ለማሰጠት ጥረት እያደረገ ነበር። ጥረቱን ለማጠናከር በተደረገው መቀራረብ አስረጂ እንዲሆን የመታሰቢያ ፎቶ ከጠላቶቻቸው ጋር ተነስተዋል። ዝርዝሩ እዚህ ጠቃሚ አይደለም ፣ የፅሁፌ አላማም ይህ አይደለም። ለማለት የፈለኩት የተለያየ ፖለቲካ ብቻ አይደለም አጥፊ እና ጠፊ የሆኑ የፖለቲካ ሀይሎች ሳይቀሩ ተቀራርበው የሚወያዩበት አጋጠሚ ብዙ ነው። ከተራ ተርታ አመለካከት ዘለል ብለን ጉዳዩን ካጤነው የራስን አላማ ከግብ ለማድረስ ከተቀናቃኝ ወገን ጋር ሳይቀር ቀርቦ መነጋገር ብልህነት እና ሲሰራበት የቆየ ጉዳይ መሆኑን ለማመልከት ጭምር ነው።

የኢሕአፓ ጥንስስ ጦር አረብ አገር ሰልጥኖ ሲያበቃ ወደ አሲምባ የመጣው በአቶ ኢሳይያስ መልካም ፈቃድ እና ሙሉ ድጋፍ መሆኑን መሪዎቹ ዘንግተውት ይሆን? አቶ ብርሀነ መስቀል ረዳ ከሻቢያ ጦር አበጋዞች ጋር ሲነጋገር የሚያሳይ ፎቶ እስካሁን ባናይም ታሪኩ ግን እውነት መሆኑን ቦታው የነበሩ ፅፈውታል። ደብተራው ይቺን ፎቶ ‘እንደምንም’ አፈላልጎ ቢለጥፍልን መልካም ነበር- ብዙ እንድንማር ይረዳናል።

ወደ ተነሳሁበት ጉዳይ ልመለስና እነ ዶር ያዕቆብ ፎቶ ተነሱ ተብሎ ከበሮ የሚደለቀው ከነማን ጋር ነው። ከዶር ነጋሶ ፣ ከአቶ ስዬ ወይም ከኤርትራው አምባገነን አቶ ኢሳይያስ? ከመጨረሻው ልጀምር - ብዙዎቻችን ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል ናት ፣ በሸፍጥ እንደትገነጠል ሆኗል እንላለን። ኤርትራን በመገንጠል ረገድ መሪ ሚና ከተጫወተው ግለሰው ጋር ሀሳብ ለመለዋወጥ ዕድል ከተገኘ በዚህ አጋጣሚ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎት (ኤርትራዊውን ጨምሮ) እንበለ-ሕግ መረገጡን ደጋግሞ ለማስገንዘብ ቢቻል ምኑ ላይ ነው ስህተቱ። አቶ ኢሳያስ በጠመንጃ እና በደም የፃፉት የፈጠራ ቅኝ ግዛት ታሪክ ግዜውን ጠብቆ እንደሚጋለጥ ማሳወቅ የሚቻልበት አጋጣሚ ከተፈጠረ መጠቀሙ ክፋት አለው? እርግጥ ፎቶ ደረቅ ነው ፣ ምን እንደተነጋገሩ አይገልፅም። ቢያንስ ቢያንስ የውይይታቸው መንፈስ ከፖለቲካ ድባብ የራቀ እንዳልሆነ ግን መገመት የሚቸግር አይደለም። ዶር ያዕቆብ ከአቶ ኢሳይያስ ጋር ስለ ጨዋራ ሕመም ወይም አምባሻ እንዴት እንደሚዘጋጅ እየተነጋገሩ ነው ብሎ የሚገምት ካለ እኔ አላውቅም።

ሌላው - ከነ ዶር ነጋሶ ወይንም አቶ ስዬ ጋር ፎቶ መነሳት ምኑ ነው ጥፋቱ? ዶር ነጋሶ ወይንም አቶ ስዬ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸው መፋቁን እስካሁን አልሰማንም። ማለት - ዛሬም የኢትዮጵያ ጉዳይ ይመለከተናል ብለው ቢቆሙ እና ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር ስለ አገራቸው አንስተው ውይይት ቢያደርጉ ስህተቱ ምን ላይ ነው? እነ አቶ ስዬ ትናንት ያራመዱት አቋም ከአገር ዘለቂ ጥቅም አኳያ የማያዋጣ መሆኑን ብቻ ሳይሆን ትክክል አለመሆኑን ጠንቅቀው ቢገነዘቡ እና እርምጃቸውን ከህዝብ እና ከእውነተኛው የአገር ጥቅም ተሚጋች ወገን ጋር ለማድረግ ቢወስኑ እንደ ጥፋት የሚቆጠር ይሆን? ከነኝህ ኢትዮጵያውያን ጋር ፎቶ መነሳት በነሱ ጫማ እንደመራመድ ይቆጠራል ያለውስ ማነው? ፎቶ የማንን አቋም ሲቀይር አይተናል? የስታሊንን ወይስ የቸርችልን? የሁድ ባራክን ወይንስ የያሲር አራፋትን? አረ ልብ እንግዛ።

አንድ ሰሞን ድረ-ገፆችን አጣቦ ፤ ፓልቶኮችን አጥለቅልቆ የነበረው መሪ ሀሳብ ‘ብሔራዊ ዕርቅ’ ለማምጣት ሁሉም ተቀናቃኝ ዜጋ (የወያኔን መሪዎች ጨምሮ) ተግቶ እነዲሠራ የሚደረገው ጥሪ ነበር። ብሔራዊ ዕረቅ ሌላ ትርጉም ከሌለው በስተቀር በአገራችን ጉዳይ ላይ ሁሉም ተቀናቃኝ ወገን ተቀራርቦ እንዲመክር የሚጋብዝ ጥሪ ነው። የነ ዶር ያዕቆብ ፣ አቶ ስዬ እና ዶር ነጋሶ ብሎም ሌሎች ተቀራርቦ መወያየት ለብሔራዊ ዕርቅ ጥሪ እንደ ጥንስስ ሆኖ የማያገለግልበት ምክንያት ይኖር ይሆን? ብሔራዊ ዕርቅ ሁሉንም የፖለቲካ ሀይሎች ማሳተፍ እንደሚኖርበት የማይስማማ አለ ብዬ አልገምትም። ይህን ታላቅ ቁምነገር ለመጀመር የተወሰኑ ዜጎች አንድ እርምጃ ወስደው ቢያሳዩን ክፋት ያለው አይመስለኝም። ሽህ ኪሎ ሜትር ለመጓዝ አንድ ብሎ መጀመር የግድ ነው።

አገራችን ከወያኔ ጎጠኛ ፖለቲከ ነፃ እንድትሆን ለማስቻል ኢላማውን ያልሳተ የፖለቲካ ስትራቴጂ ያስፈልገናል። ኢላማ መኖሩን ማወቅ ብቻ በቂ አይደለም። ኢላማው ላይ ሳያነጣጥር ተኩስ የሚከፍት ወታደር አላፊ አግዳሚውን ከማቁሰል ብሎም አዳዲስ ጠላት ከማፍራት ሌላ ለድል ሊበቃ አይችልም። ደካማ ወታደር በእሩምታ ተኩስ ጥይቱን ጨርሶ ምርጫው እጅ መስጠት ብቻ ይሆናል። ፖሊቲካውም እንደዚያ ነው - የፖለቲካ መድረክ ላይ ነኝ ብሎ ግብ ላይ ያላነጣጠረ ተግባር ላይ ማተኮር ጉዳቱ ለራስ ነው። ከጭፍንነት ሌላ በጠላት ዘንድም ያስገምታል።

በዜግነቴ ይበጃል ያልኩትን አስተያየት ሰጥቻለሁ። እነ ዶር ያዕቆብ እራሳቸውን ለመግለፅ የሚሰንፉ ሆነው አይደለም ይህን ሀተታ የፃፍኩት። ነገሩ የግል ጉዳይ ካለመሆኑም በላይ ለዚህ አይነቱ ርካሽ ፖለቲካ ግዜ ያላቸውም አይመስለኝም። እኔም ቢሆንልኝ ኖሮ ወያኔ እያደረሰ ባለው አገር የማጥፋት ጉዳይ ላይ ያተኮረ አስተያየት ብቻ ብጭር ምንኛ ደስ ባለኝ።

ከገደል ላይ ቁልቁል እየተወረወረ ታች ከተነጠፈው ድንጋይ ጋር የሚላተመው ጅረት በሚፈጥረው አስገምጋሚ ጩኸት የተረበሸው መንገደኛ ቀረብ ብሎ -
“ውሀ ምን ያስጮህሀል? ቢለው - ድንጋይ ፣
ድንጋይስ ምን ያስጮህሀል? ቢለው - ውሀ” የሚል መልስ አግኝቶ እንቆቅልሹ ሳይፈታ ጉዞውን ቀጥሏል። እኛስ ከነ እንቆቅልሻችን የምንጓዘው እስከ መቼ ይሆን?